# <u>የትግሉ አቅጣጫ ደብዛው ሲጠፋ! በሳይንስ ያልተደገፈ ትግል ግቡን አይመታም !!</u>

<u>መግቢያ</u>

የግንቦቱ 1997 ምርጫ ውጤት በወያኔ አገዛዝና በግብረ አበሮቹ ከተነጠቀ ወዲህ በምርጫው ውጤት የፈነደቀው ፣ በተለይም በተቃዋሚው ሰፈር የተሰለፈው ኃይል ዛሬ ከፍተኛ ፈተና ውስጥ ወድቆና ርስ በርሱ ሲነካከስና ሲወነጃጀል አልፎ አልፎ ይሰማል። ያ እንደዚያ ደምቆ የነበረው ስምምነትና እጅ ለእጅ ተያይዞ በአንድነት መጓዝ ወደ ጎሪጥ ወደ መተያየትና ወደ ማያስፈልግ ሽኩቻዎች እየተለወጠ ህዝባችንን አንቆ ለያዘው አምባገነናዊ አገዛዝና ተባባሪዎቹ እንዲጠናከር በር እየከፈተለት መጥቷል። የወያኔን አገዛዝ እንደሬት መረረኝ እያለ የሚጠላውና እዚህና እዚያ ተሰበጣጥሮ ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ ጩኸቱን የሚያሰማው የተወሰነው ኃይል በዚህም በዚያም ምክንያቶችን እየፈለገ የግንቦቱ ምርጫ ውጤት የተወሰኑ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ትግል ውጤት አድርጎ ለማስቀመጥ የማያደርገው ሙከራ ይህ ነው አይባልም። በዚህም ምክንያት አንድ የተወሰነ አክራሪ ቡድን በጥናትና በዕውቀት የተደገፈ ትግል ከማካሄድ ይልቅ እዚህና እዚያ በማቅራራት ብዙ ሰዎችን እያሳሳተ የትግሉን አቅጣጫ በማዛነፍ ላይ ይገኛል። ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ የኢትዮጵያ ህዝቦች የወደፊት ዕድል ለረጅም ዐመታት ተንጠልጥሎ መቅረቱ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ የቲዎሪና የሳይንስ ጥራት ሳይኖራቸው የትግሉን አርማ በመንጠቅ የቦዘኔያዊ ዓላማ እንዲኖረው በማድረግ የዛሬው አገዛዝ ቢወደቅ እንኳ እነዚህ ኃይሎች ድብቅ ዓላማቸውን እውን በማድረግ የኢትዮጵያን ውድቀት በሌላ መልክ እንደሚያፋጥኑ ግልጽ መሆን አለበት።

የግንቦቱ ምርጫ ውጤት የጥቂት ግለሰቦች ወይም የአንድ ቡድን ድል አይደለም። የግንቦቱ ምርጫ ውጤት ከ95% በላይ የሆነው ፣ ዲሞክራሲንና ብልጽግናን እንዲሁም በእኩልነትና በመፈቃቀር ላይ የተመሰረተ አንድነትን የሚሻው ህዝባችን ውጤት ነው። ከምርጫው በፊት ቀደም ብሎ የተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍና እንዲሁም ደግሞ የምርጫው ቀን ህዝባችን ግልብጥ ብሎ ሲወጣ ያመለከተው ጥቂት ግለሰቦችን እንዲያው ስልጣን ላይ ለማውጣት ሳይሆን ፣ በተወሰነ ዲሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥና ለጊዜው ይሻላሉ በሚላቸው ድርጅቶች አማካይነት ፍላጎቴን አሟላለሁ ፣ ሰላምንና ብልጽግናን አገኛለሁ በማለት ነው። በዚህም መሰረት በተለያዩ የዛሬውን አገዛዝ በሚቃወሙ ኃይሎች መሀከልም የጋራ ስምምነት ተፈጥሮ በአገሪቱ ውስጥ አንድ ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲዳብር ለማድረግ ፣ ለዚህ ሆነ ለዚያኛው ኃይል ብቻ ስልጣን ይገባዋል በማለት የማያስፈልግ ሽኩቻ ውስጥ ለመግባት አይደለም። በተለይም እኛ ዲሞክራቶችና የተገለጠልን ኃይሎች ከግንቦቱ ምርጫ ውጤት የተረዳነው ቁም ነገር ቢኖር ይህንን መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ይኸውም በፕሪንስፐል ላይ የተመሰረተ አንድነትንና ትብብርን መስርቶ ዲሞክራሲያዊ ባህልን በማዳበር በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ ግንባታ ማካሄድ።

ዛሬ በአንዳንድ አካባቢ እጅግ ባህል በጎደለው መልክ የሚካሄደው መራወጥ ግን የግንቦቱን ምርጫ ውጤትና መንፈስ የሚጻረር ነው። አንዳንድ ያልተገሩ ሰዎች እየተነሱ በተወሰነ ድርጅት አማካይነት የግንቦቱን ምርጫ ውጤት ለመንጠቅና ህዝባችንን በማሳሳት ገደል ውስጥ እንዲገባ የሚያደርጉት መራወጥ ዝም ብሎ መታየት የለበትም። በታሪክ ውስጥ እን ደታየው የቲዎሪና የሳይንስ ጥራት የጎደለው ፣ በስሜትና በአለሁ አለሁ ባይነት ላይ የተመሰረተ ትግል አንድን ህዝብ ወደ ድልና ወደ ብልጽግና ሊያመራ በፍጹም አይችልም። ከናይጀሪያውና ከኬንያው ምርጫ ፣ እንዲሁም ከደቡብ አፍሪቃው የአፓርታይድ አገዛዝ መደምሰስ በኋላ የምናየው ሁኔታ ይህንን ነው።

የዛሬውን በተቃዋሚው ሰፈር ያለውን መሻኮት ለመረዳት አንዳንድ መሰረተ ሃሳቦችን አንስቶ መወያየት እጅግ አስፈላጊ ነው። አደባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ እንደሚባለው

አነጋገር ነገሮችን እያብላሉ የተነሱትን ችግሮች እየመረመሩና ችግሮችም ለምን እንደተነሱ ጥያቄ እያነሱ መልስ ለመሰጠት መጣር የምሁሮች ተግባርና ሃላፊነት እንደመሆኑ መጠን መሰረተ ሃሳቦችን እያነሳሁ አንባቢን ለማወያየት እሞክራለሁ። በዚህም ጥረቴ ሌሎችም እንደሚታከሉና ለችግራችን መፍትሄ የበለጠ ጥራትን ለመሰጠት የበኩላቸውን አስተዋጽዎ እንደሚያደርጉ ተስፋ አደርጋለሁ።

## የወያኔ ስልጣን ላይ መውጣት ያስከተለው የኃይል አሰላለፍ ለውጥ !

እንደሚታወቀው ወያኔና ሻይባ ስልጣን ላይ ለመውጣትና የዛሬውን እጅግ የተሰበጣጠረ ሁኔታ ሊፈጥሩ የቻሉት በተለያዩ ምክንያቶች እንደሆነ ቀደም ብለው በወጡ ጽሁፎቼ ላይ ለማሳየት ሞክሬያለህ። ብዙ ታጋይ ነን የሚሉ ዛሬ ነገሮችን ገነጣጥለውና ቆነጻጽለው ለማስቀመጥ እንደሚሞክሩት ሳይሆን ወደድንም ጠላንም አንድ መጥፎም ሆነ ደግ አገዛዝ ከሰማይ እንደ ታሪክ አጋጣሚ ሊወርድ  በፍጹም አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ አጋጣሚ ሁኔታዎች በመሰበጣጠር ለአንድ መጥፎም ሆነ ጥሩ አጋዛዝ ስልጣን ለመያዝ መንገዱን ያመቻቹለታል። በአንድ ህዝብ ውስጥና በአንድ የታሪክ ወቅት የሚከሰቱ የኃይል አሰላለፎች የዚያ ህብረተሰብ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ባህላዊ ፣ ህብረተሰባዊ ፣ ባህላዊና የታሪክ ሂደት ወጤትና አወቃቀር ነጸብራቆች ናቸው። አንድ ህብረተሰብ የረጅም ጊዜ የባህል ፣ ውስጥ ለውስጥ ሲብላላ የሄደ የምሁር ክርክርና የኢኮኖሚ ግንባታ ባህል ካለው ከውስጡ ፈልቀው የሚወጡ ኃይሎች የበሰሉ ፣ ታሪክን የተገነዘቡና ህብረተሰብአዊ ኃላፊነትን በመቀበል ህብረተሰቡ ተከታታይነት እንዲኖረው በጸና መሰረት ላይ እንዲገነባ ለመጪው ትውልድ ፈር አሲይዘው ታሪክን ሰርተው ያልፋሉ። ይህ ሆኔታ በሌለበት ፣ ህብረተሰቡ በሳይንስ ላይ የተመሰረተ የባህል እንቅስቃሴ አድርጎ በማያውቅበት ህብረተሰብ ውስጥ ፣ ጮሌዎች ፣ ታሪክን ያሚያበላሹ ፣ ህብረተሰቡን በማዋከብ በውዥንብር ዓለም ውስጥ እንዲኖር በማድረግ እጣው ዘለዓለማዊ ድንቁርናና ረሀብ እንዲሆን የሚያደርጉ ኃይሎች ስልጣን በመያዝ ሁኔታውን እንደሚያባብሱ በብዙ አገሮች ታሪክ የታየ ነው። በሌላ አነጋገር የአንድ አገዛዝ ክፉም ሆነ ደግ ስራ ፣ የአንድ ህብረተሰብ ንቃተ-ህሊናና የባህል ዕድገት ደረጃ ወጤት ነው። አንድ አገዛዝና በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚከሰት ኃይል አሰላለፍ በምንም ዐይነት ከዚህ ወጭ ሊሆን አይችልም።

ስለዛሬው በአገራችን ውስጥ ስለሰፈነውና ህዝባችንን ስለሚያተራመሰው አገዛዝ የሚሰጠው ትርጉም ግን በፍጹም ከታሪክ ፣ ከብዙ አገሮች ልምድና ከሳይንስ ጋር የሚጣጣም አይደለም። የሚሰጡት ትርጉሞች በሙሉ የነገሮችን ሂደት በሚገባ እንዳንረዳ የሚያደርጉን ብቻ ሳይሆኑ ወደ ፊትም ታሪክ መልክ ባለው መንገድ እንዳይሰራ የሚያደርጉ የተዛነፉ አስተሳሰቦች ናቸው።  የዛሬውን አገዛዝ ባህርይና ተግባር ከህብረተሰብአችን የረጅም ጊዜ የታሪክ አወቃቀር ጋር ካልተያያዘ ሌሎች ኃይሎች በዲሞክራሲ ስም ስልጣን በመያዝ ሁኔታውን ሊያባብሱት እንደሚችሉ የብዙ አገሮች ታሪክ ልምድ እያሳየን ነው።

የዛሬው አገዛዝ የባህላችንና የታሪካችን ወጤት ነው ብልን አምነን ከተቀበልን ፣ ስልጣን ለመውጣት ደግሞ በጊዜው በአገራችን የተከሰተው አብዮታዊ ሁኔታና መተረማመስ ፣ በየጊዜው ይታይ የነበረው የተመሰቃቀለ ኃይል አሰላለፍ ለውጥ ፣ በአብዮቱ ወቅት ተዋናይ የነበሩ ኃይሎች የታሪክ ግንዛቤ ጉድለትና የታሪክን ሃላፊነት ለመቀበል አለመዘጋጀት ፣ ወይም ደግሞ የተዘጋጁ ኃይሎችን ለማጨናገፍ ወዲህ ወዲያ መሯሯጥ ፣ የማያስፈልግ መናናቅ- ይህ ጉዳይ ዛሬም ያለ ነው- እኔ ካልመራሁት ብሎ አጉል ግብ ግብ ውስጥ መግባት ፣ ሰፋ ላለ ሳይንሳዊ ክርክር አለመዘጋጀት ፣ ወይም ደግሞ ከሳይንሳዊና ከቲዎሪ ትግል ይልቅ ኃይልንና ሀብትን ወደ ሚጨረስ አጉል ግብ ግብ ማምራትና እኛ እንደ ህብረ-ብሄር እንዳንቋቋም የውጭ ኃይሎች ባጠመዱልን ወጥመድ ውስጥ ገብተን መንደፋደፍ ፣ እነዚህ ሁሉ የየበኩላቸውን አስተዋጽዎ እንዳደረጉ የማይታበል ሀቅ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ እንደዚህ

ዐይነቱ አገርን የሚያተረማምስ ኃይል ስልጣን ይጨብጣል ብሎ የገመተም ሆነ ሊገምት የሚችል ማንም አልነበረም። ይሁንና ግን የየካቲቱ አብዮት መተረማመስ በፍጹም ወደ ህብረተሰብአዊ መደላደልና መረጋጋት እንደማያመራም ደግሞ ግልጽ ነበር። ለኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት እንታገላለን የሚለውን ኃይል ትተን ታሪክን በተሳሳተ መልክ እየተረጎመ ከውጭ ኃይሎች ጋር በማበር ብሄረ-ሰቦቹን ነፃ አወጣለሁ ብሎ እዚህና እዚያ የሚራወጥ ኃይል ለረጅም ጊዜ ችግርን እንደሚፈጥር ፣ ይህንንም ባህል በማድረግ ታሪክ እንዳይሰራ በማተራመሱ እንደሚቀጥልብት ከመጀመሪያውኑ የታወቀ ጉዳይ ነው። ባጭሩ ለዛሬው አገዛዝ ስልጣን መውጣት ሳናውቅ እኛ የታሪክን ሂደት በደንብ ያልተገነዘብን ኃይሎች ሁሉ በተለያየ መልክና ጥንካሬ አስተዋጽዎ አድርገናል ማለት ይቻላል። ይህንን ስንገነዘብ ብቻ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ አወቃቀር ፣ የታሪክ ሂደትና በተለያየ ወቅት ብቅ የሚሉ ኃይሎች ለምን ይህንን ወይም ያንን የመሰለ ፖለቲካ ሊያካሂዱ ይችላሉ ብለን መረዳትና ከታሪክ መማር እንችላለን ።

ከዚህ ስንነሳ የወያኔ ስልጣን ላይ መውጣት አዲስ የኃይል አሰላለፍ ብቅ እንዲል የግዴታ አግዟል። በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ የተሳተፈው በጊዜው በቂ ዕውቀት የነበረው ኃይል አንድም በራሱ ሽኩቻ በመመታቱ ፣ በሌላም የታሪክን ሂደት ያለተገነዘቡ በደርግና ከደርግ ጋር ባበሩ ኃይሎች በመሟጠጡ የፖለቲካው መድረክ አንዳንድ የፖለቲካ ንቃተ ህሊናቸው እዚህ ግባ በማይባሉ ኃይሎች ሊነጠቅና የተዋናይ ሚናውን ሊወስዱ አስችሎአቸዋል። እነዚህ ከዚህ በፊት ከህዝብ ጎን ቆመው የማያውቁ ፣ የህዝብን ብሶት አንድም ቦታ ላይ በጽሁፍም ሆነ በንግግር አንስተውም ሆነ አነጋገርው የማያውቁ ግለሰቦች የጊዜውን የኃይል አሰላለፍ በመረዳትም ሆነ የታሪክ አገጣሚ በፈጠረላቸው መድረክ በመጠቀም ፣ ከዚህም ከዚያም የተሰበሰበውን ኃይልና ምንም ዐይነት የፖለቲካና የህብረተሰብ ግንባታ ዕውቀት የሌለውን ሁሉ በዙሪያቸው ለማሰባሰብ ችለዋል። ወያኔ የጀመረው የክልልና አገርን የማፈራረስ ፣ እን ዲሁም ደግሞ ኤርትራን ማስገንጠል እነዘህን ሳይንሳዊና የቲዎሪ መሰረት የሌላቸውን ኃይሎች በታወቁ ግለሰቦች ዙሪያ እንዲሰበሰቡ አስችሏቸዋል ማለት ይቻላል። ከዚህም በመነሳት እነዚህ ታዋቂ ግለሰቦች ፣ ከፖለቲካ ብስለት ጋር በማጣመር ሳይሆን በችኮላና አንድ ፓርቲም ሆነ ድርጅት ህብረተሰብአዊ ሃላፊነት እንዲወስድ ሳይንሳዊ ጥናት ከመጀመሪያውኑ ማካሄድ እንዳለበት ሳይረዱ ወደ ፓርቲ ምስረታ በማምራት ብዙ የተወናበዱና እጅግ ኋላ ቀር አመለካከት ያላቸውን ፣ በጮሌነታቸውና ነገርን በማቀላጠፍ ብቻ የታወቁ ግለሰቦችን ማሰባሰብ ችለዋል ማለት ይቻላል። የተማሪው እንቅስቃሴ መመታት ፣ የምሁሩ መሟጠጥ ፣ መዳከምና መበታተን የፖለቲካንና የህብረተሰብ አገነባብ ሂደት በቅጡ ባልተገነዘቡ ፣ የውይትትም ሆነ የጥናት ልምድም ሆነ ገት በሌላቸው ኃይሎች ቀስ በቀስ የፖለቲካው መድረክ ሊነጠቅ ችሏል። ይህ ሁኔታ ደግሞ የግዴታ ፊዩዳለዊ ባህርይ በመወሰድ ፣ ከህብረተሰብአዊ ውይይት ይልቅ ግለሰብን ወደ ማምለክ ለማምራት ችሏል። የፖለቲካ ንቀታ ህሊና የሌለውና ታሪክ እንዴት እንደሚሰራ ያልተገነዘበው ኃይል ሁሉ በአንዳንድ ስማቸው ለጊዜው በገነኑ ኃይሎች ስር በመመሸግ የትግሉን መስመር ለማዛነፍና ወደ ውጭ የህብረተሰብ ጥያቄዎችን አስታኮ ውይይት እንዳይካሄድ አግዷል። ይህ ኃይል ከነቁ ኃይሎች ይፈልቁና ይሰነዘሩ የነበሩ ሃሳቦችን በማንቋሸሽ ወይም ደግሞ እንዳልተሰነዘሩ አድርጎ በመውሰድ ግለሰቦችን በማሳደድ የፖለቲካን ትግል ወደ ማድበስበስ አመራ።

በአለፉት አስራ አምስት ዐመታት ብቅ ያሉትንና ዝናን ያገኙትን ፓርቲዎችና ግለሰቦች ስን መረምር የምንደረስበት ውጤት መፈክር አንሰተው በእልክ ከመታገል በስተቀር ብስለት ያለው ታሪካዊ ትንተና በመስጠት የነቃ ትግል ለማካሄድ አለመቻል ነው። ከተማሪው እን ቅስቃሴ የተረፈው ኃይል ደግሞ በአዲሰ መልክ ለመደራጀት እጅግ ችግር ውስጥ ገብቶ ነበር። አንደኛ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ የተፈጠረው አጉል ሽኩቻና መተላለቅ ከኮሙኒዝምና ከማርክሲዝም ጋር በመያያዙ እነዚህን ተንጠባጥበው እዚህ የደረሱ ኃይሎችን በቀላሉ የሚቀበላቸው ኃይል አልነበረም። በሌላ ወገን ደግሞ እነዚህ ከተማሪው እንቅሰቀቃሴ ተንጠባጥበው የቀሩ ኃይሎች ከድሮ የታሪክ ፣ የሳይንስና የቲዎሪም ሆነ የተግባር ስህተት ትምህርት ቀስመው በአዲስ መልክ ለመደራጀት በፍጹም አቅም አልነበራቸውም። አንዳንዶቹ

በድሮ ሀልም ስለሚኖሩ ከሚታፊዚክስ አንፃር ሊደረግ የሚገባውን ጥናትና ትንተና እንዲሁም ደግሞ አዲስ የአደረጃጀት ስልት በማዳበር እንደገና በአዲስ መንፈስ ከመነሳት ይልቅ ፣ ለእነዚህ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ስር ፣ ግን ደግሞ ፖለቲካ እንዴት እንደሚሰራ ላልተገነዘቡና ለመገንዘብም ለማይፈልጉ ኃይሎች መድረኩን የግዴታ እንዲለቁ ተገደዱ። በዚያው መጠንም አንዳንድ ከሰላሰና አርባ ዐመት መኝታቸው የተቀሰቀሱ የሚመስሉ ኃይሎች የፖለቲካው መድረክ ውስጥ በመሳተፍ የነቁና የታሪክን ሂደት በሌላ መልክ የሚረዱ ግለሰቦችንም ሆነ ድርጅቶች በር መዝጋት ቻሉ። የእነዚህ አዳዲስ ኃይሎች ብቅ ማለትና የፖለቲካውን መድረክ መያዝ እዚህና እዚያ ተበታትነው ግራ ገብቷቸውና የዓለም ነገር ጨልሞባቸው ላሉ ምስኪን ኢትዮጵያውያን መጠለያ መንገድ ከፈተላቸው። ስም ያለው ፣ የተማረ ሁሉ ፖለቲካን ያካሂድ ይመስል ፣ ህብረተሰብን ለመገንባት የሚያስችል ዕውቀት ያለው ይመስል ፣ ተምረናልና ዝና አለን የሚሉ ኃይሎች ምንም ግንዛቤና ሰፊ ጥናት ሳያደርጉ ብዙ ሰዎችን በዙሪያቸው ለማሰባሰብና በዚያውም ከምስኪኑ ድሀ ገንዘብ በመሰብሰብ ትግል እናካሄዳለን ማለት ጀመሩ። ይህ ሁኔታ የነቁ ኃይሎችን የባሰ እየዋጣቸው ፣ የሚያሰሙት ጩኸት ሁሉ እንደ እብድ ጩኸት እየታየ ለጊዜውም ቢሆን ተረግጠው ቀሩ። እንደነ ልደቱ አያሌው ፣ እንደነ ዶክተር በየነ ጴጥሮስና ሌሎች ስማቸውን ለመጥራት የማልፈልገው የዚህ የኢትዮጵያ የተተራመሰና የአዳመ ህዝብ ግራ መጋባት ውጤቶች ናቸው ማለት ይቻላል።

የአለፉትን አስራ አምስት ዓመታት የጭቆናና የትርምስ ሁኔታ ስንመረምር የምንገነዘበው እነዚህ ብቅ ብለው ዝናን በአጭር ጊዜ ለመጎናጸፍ የቻሉ ኃይሎች ለስልጣን የመታገላቸውን ያህል ስለ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ፣ የባህል ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ሁኔታ  አንድም ቦታ ላይ አመርቂ ጥናትና የአገራችንንም የተወሳሰበ ትግል እንዴት እንደሚፈታ ችሎታቸውን አለማሳየት ነው። አብዛኛዎቹ ችግሩ እንዴት እንደመጣና እንዴትስ እንደሚፈታ ከማሳየት ይልቅ ቶሎ ብለው ፕሮግራም በመጻፍና በመበተን በቀላሉ ሰው ሊያሰባስቡና ስልጣን ሊወጡ የሚችሉ መስሎ ታያቸው። በነቁና ከተገለጸላቸው የሚሰነዘሩትን ሳይንሳዊ አመለካከቶች እየረገጡ ታዋቂነታቸውን በየዋሁ ዘንድ አረጋገጡ። በዚህም ብዙ ሰዎችን ማሳሳት ብቻ ሳይሆን እዚያው ደንቁሮ እንዲቀር አደረጉ። ይህ ታሪክ ይቅር የማይለው አደገኛ ስልት ነው። ምክንያቱም በየትኛውም ታሪክ ተሰራበት በሚባል አገር ውስጥ ሁሉ ፕሮግራም አውጥቶ ከመበተን በፊት የቲዎሪና ሳይንሳዊ ክርክር ማካሄድ የማይታለፍ መሰረታዊ የህብረተሰብ ግንባታ ዘዴ በመሆኑ ነው።

ከዚህ ስንነሳ ፣ የኢትዮጵያ የመንግስት አመሰራረትና አወቃቀር ጉዳይ ከታሪክ አንጻር ፣ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ኋላ መቅረት ጉዳይ ፣ የህብረ-ብሄር አመሰራረት ጉዳይ ፣ የብሄራዊ ነፃነት ጉዳይ ፣ ከዚህም በመነሳት ኢትዮጵያን በምን መሰረተ ሃሳብና የማቴሪያል መሰረት ላይ ነው መገንባት የሚቻለው ፣ ስለሆነም ምን ዐይነት ህብረተሰብ ነው መመስረት ያለብን የሚለውና ግለሰብአዊ ነፃነትንና የዲሞክራሲያዊ መሰረተ ሀሳቦች ውይይት ሳይደረግባቸው ቀሩ። ምክንያቱም ፣ በአንዳንድ አፈጮሌዎች አባባል የታወቁ ግለሰቦች እጅግ ተዝቆ የማያልቀውን ችግር በተአምራቸው ይፈቱታል የሚል ነው። ይህ መተረማመስ በእንደዚህ አን ዳለ ነው የግንቦቱ  ምርጫ ልዩ ሁኔታን የፈጠረው።

ምርጫውም ሆነ የምርጫው ውጤት የዛሬውን አገዛዝ እንቃወማለን በምንል ሰዎች ዘንድ ሁሉ አዲስ መንፈስ እንደፈጠረ የታወቀ ጉዳይ ነው። መፈቃቀር ፣ መተሳሰብ ፣ አንድ ላይ ሆኖ እጅ ለእጅ መጓዝ ፣ ከዚህ በፊት የነበሩትን የውስጥ ለውስጥ ሽኩቻዎች በሙሉ አሽቀን ጥሮ በመጣል "ለአንድ ዐላማ" በመነሳት ወደ ፊት መራመድ ነበር። ሁሉም በቅንጅት አካባቢ የተሰበሰበ ነበር። ብዙም መሰረታዊ ጥያቄዎች አይነሱም ነበር። ጊዜውም አይፈቅድም ነበር። የሁሉም መንፈስ አንድ ስሜት ነበረው። ከፖለቲካው ጥራት ባሻገር የዛሬውን አገዛዝ በዚህም በዚያም ብሎ መጣል። በሌላ ወገን ደግሞ ሁኔታውን ጠጋ ብሎ ለተመለከተው አንድ ዐይነት የጭንቀት መንፈስ ይታይ ነበር። የዛሬው ሁኔታ ቢፈታስ ችግሩን እንዴት እንወጣዋለን የሚል ነው። ከአንዳንዶች የሚሰጠው መልስ ካልብዙ ውጣ

ውረድ የግለሰቦችን ስም መጥራት ፣ ወይም ደግሞ በደፈናው ቅንጅት ይመልሰዋል ወይም ይፈታዋል የሚል ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ቅንጅት እስከተወሰነ ደረጃ ድረስም አንዳንድ መልስ መስጠት እንደሚችል ባያጠራጥርም ፣ ጥያቄው ግን የሚሰጠውና ተግባራዊ የሚሆነው መልስ ኢትዮጵያን እንደ አንድ ህብረ-ብሄርና ህብረተሰብ ሊያዋቅራት የሚያስችል ነው የሚለው ነው። በአንዳንዶቻችን ዘንድም የነበረው ችግር ይህንን የመሳሰለውን ጥያቄ አንስቶ ለመከራከር ፣ ለማስተማርና ለማስረዳት ያለመቻል ነው። ዕውቀቱም ሆነ ችሎታውም ቢኖር እንኳ ለማዳመጥ የሚፈልጉ ኃይሎች በፍጹም የሉም። በእንቅስቃሴቅው ውስጥ በዕውቀታቸው ፣ በችሎታቸውና በአመለካከታቸው የተለያዩ ግለሰቦች በመኖራቸው ፣ በዚህ ላይ ደግሞ እዚህና እዚያ የሚቅለበለቡ ኃይሎች መድረኩን በመያዛቸው ለሚነሱት ጥያቄዎችና ጥርጣሬዎች መልስ ለመስጠት አሰቸጋሪ ነበር። ክርክር ያልተለመደብት ህብረተሰብ ፣ ወደ ፊት ከመጓዝ ይልቅና ነገሮችን ከሁሉም አቅጣጫ መመርመርና ማገናዘብ ባልተለመደብት ማህበረሰብ ፣ ሳይንሳዊ ክርክር ወደ ሰይጣን አቀራረብ በሚመስልበት ፣ ይኸኛውም ሆነ ያኛው ኃይል በተግበሰበሰበት ውስጥ የበታች ሆኖ ከመቅረትና ከመዋጥ በስተቀር ሌላ አማራጭ አልነበረም። ይህ ሁኔታ ስር እየሰደደ ሲሄድና የግንቦቱም የምርጫ ውጤት በተለያዩ ምክንያቶች ሲቀለበስ ልዩነቶቹ ግልጽ ሆነው መውጣት ይጀምራሉ። ካለምን ም ሳይንሳዊ መሰረትና ፕሪንስፕልስ የተሰበሰበው ሁሉ በነቁ ኃይሎች ላይ ጥርጣሬውን በግልጽ ማሳየት ጀመረ። ይህ ጉዳይ ለጩሌዎች አመቺ ሁኔታዎች ፈጠረላቸው። ካለቅንጅት በስተቀር ፣ ካለ ከሌ በስተቀር ሞቼ እገኛለሁ የሚል የማያስፈልግ ክርክርና አመለካከት ብቅ ማለት ጀመረ። ግለሰቦችን ወደ ማምለክ አመራ። ለሃሳብ መለወሻ የማይሰጥ ፣ ለክርክር የማያመች ሰፊውን ህዝብ የሚያደነዝዝ ሁኔታ የፖለቲካውን መድረክ እየተቆራኘው መጣ።

በመስከረም ወር የተጠራው ስላማዊ ሰልፍ መቅረት ፣ የቤት ውስጥ አድማው በተልፈሰፈሰ መልክ መታገዱ ፣ በዚህም መሰረት ፣ በቅንጅት አመራር ዘንድ የዓለምን ፖለቲካ በሚገባ አለማጤን ፣ እንዲያው የዓለም ኮሙኒቲው በሚለው እጅና እግር በሌለው አስተሳሰብ በመታወር ጠቅላላውን የኢትዮጵያን ህዝቦች ድል ባለማወቅና የአንዳንዶቻችንን ምክር ባለመቀበል እንዲጨናገፍ ማድረግ ፣ በውስጥ ለዘብ ብሎ የነበረውን ቅሬታ ጉልህ አድረጎ አወጣው። ቅንጀት በማሸነፉ ፣ አንዳንዶቹ የመሰላቸው እኛ የነቃን ኃይሎች እንደከብት እን ደምንነዳ ነበር። ጥያቄ የመጠየቅ ፣ አንዳንድ ጥርጣሬዎች ማሳየት የማንኛውም ሰው ነኝ የሚል ፍጡር ተፍጥሮአዊ መብትና ግዴታ መሆኑን የማይረዱ ግራ የገባቸው ግለሰቦችና ጩሌዎች የጥያቂውን አነሳስ በደንብ ከማጤን ይልቅ ነገር ማጣመም ጀመሩ። ወደ ጥናትና ወደ ምርምር ከዚያም ለኢትዮጵያ ህዝቦች ወደ ሚያመቸው መልስ ከማምራት ይልቅ በሩን ወደ መዝጋት አመሩ። አሰቸጋሪ ሁኔታ እየፈጠሩ መጡ ማለት ነው። እነዚህ ግለሰቦች መሰረታዊ ውይይት ከማድረግ ፣ የአገራችንን ችግር እንዴት መፍታት እንቻለለን የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ላይ ከመረባረብ ይልቅና በጊዜው እየመላለሱ በመጠየቅ ራስን ከማሰጨነቅ ይልቅ ጥናት እንዳይጠና ፣ ሌሎች የችግራችንን ምንጭ እንዳይረዱ ሰፊ ክርክርና ውይይት እንዳይደረግ አገዱ። በነሱ አባባል የኢትዮጵያን ችግር የሚያወቁ በአመራር ብቻ እዚህና እዚያ ተሰበጣጥረው የሚገኙ እንጂ እኛ ምንም ዐይነት ዕውቀት የለንም ፤ ሰለዚህም እነሱ እስኪመጡ ድረስ አፋችንን ከፍተን እየጠበቅን መቀመጥ አለብን። በተጨማሪም ፣ በእነዚህ ግለሰቦችና የቅንጅትን አርማ በየዋህነት አንግበው በሚጓዙት አስተሳሰብ የእኛ ተግባር ገንዘብ መሰብሰብ ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግና ግለሰቦችን እያወደሱ መኖር ብቻ ነው። ትግሉ በሰላማዊ ሰልፍና ሻማ መብራት ይዞ በመቆምና ሀዘንን ማሰማት ፣ እንዲያም ሲል ገንዘብ እየሰበሰቡ ታማኝነትን ማሰማት ነው። ከዚህ ውጪ ትግል መካሄድ የለበትም የሚል ነው። ሌሎችም ቢሆኑ መሰረት ያለው አስተሳሰብና አገራችንን በጸና መሰረት ላይ ሊያቆማት በሚችል መሰረተ-ሀሳብ ላይ መወያየት አይፈልጉም የሚሉ ናቸው። በእዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ እንዴት አድርጎ መታገል ይቻላል? እንዴትስ አድርጎ ሃሳብን ማንሸራሸር ይቻላል ? እንዴትስ አድርጎ ዲሞክራሲያዊ ባህልን ማዳበር ይቻላል ? በጣም አሰቸጋሪ ጉዳይ !

ይህ ሁኔታ በዚህ እንዳለ የውጭ ቅንጅት አመራር ነኝ የሚል ከአገር ቤት ውስጥ ማንዴት ተሰጠኝ ብሎ መግለጫ ያወጣል። ይህም ጉዳይ በአንዳንዶቻችን ዘንድ ጥርጣሬን ቢያሳድርም

የአገር ቤቱ አመራር ከታሰረ ድረስ ቢያንስ የውጪውን ማህበረ-ሰብ "ሊያሰባስብ የሚችል" ኃይል በሚል ለጊዜውም ቢሆን ነገሩን ዝም ብለን ተቀበልን። ይሁንና ግን ይህ የውጭ አመራር አልፎ ተርፎ ሌሎችን ሳያማክር ፣ ብዙ ጥናት ሳያጠና ፣ መቋጠሪያ የሚገባቸውን ነገሮች መስመር ሳያሲዝ የኢትዮጵያን አንድነትና ዲሞክራሲያዊ ህልውና ሲፈታተኑ ከነበሩና አሁንም ከሚፈታተኑ ጋር የጋራ ግምባር መስርቼአለሁ ብሎ አስታወቀ። ይህ ጉዳይ በመሀከላችን ቅሬታን አስነሳ። እራሱን ቅንጅትን በጅምላ በሚደገፉ መሀከል ክፍፍልን ፈጠረ። የአገር ቤቱን አመራር ብቻ ነው የምናውቀው በሚለውና የውጪ አካል ነኝ የሚለውን በሚደግፈውና አሁን አክራሪ ሆኖ በወጣው መሀከል ልዩነት ተፈጠረ። ልዩነቱ በየ ፓል ቶክ በደንብ መንጸባረቅ ጀመረ። እጅግ አሰቸጋሪ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ መጡ ማለት ይቻላል። በተጨማሪም ራሱ በውጪው አመራር እጅግ በአስቂኝ መልክ የተፈጠረው መከፋፋል ፣ ዲሞክራሲያዊ ባህል የጎደለው አሰራርና ቀጠፋ ትግሉን ሊያዳክመው ቻለ። እነዚህ አመኔታ የማይጣልባቸው ናቸው ወይ አገር የሚመሩት ብለን ጥያቄ ማቅረብ ተገደድን። ይህ አጠቃላይ አለመግባባትና መወነጃጀል በየመነጋገሪያው መድረክ መንጸባረቅ ጀመረ። አዲስ የተፈጠረው መድረክ ወደ መቧረቂያነት ተለወጠ።

ዛሬ በግልጽ እንደምናየው ይህ የውጪ አመራር የሚባለውን ብቃትነቱን የሚያሳይ ፖለቲካ ሲያራምድ አይታይም። አልፎ አልፎ መግለጫ ከማውጣት በስተቀር በዛሬው አገዛዝና በውጪ ኃይሎች መሀከል ያለውን ትስስር ፣ ከዚህም በመነሳት በህዛባችን ላይ የተጣለውን የጭቆና ግፍ ፣ የድህነትና የአገራችንን ህልውና መዳካም እየተነተ ለህዝባችንም ሆነ ውጪ አገር ለሚኖረው ኢትዮጵያዊ ማመልከትና የትግሉም አቅጣጫ እንዴት መሆን እንዳለበት መጠቆም አልቻለም። እንዲያውም ይባስ ብሎ ብሄራዊ ነጻነትና በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ለህዝባችን አለኝታ የሚሆን ጠንካራ ኢኮኖሚ በውጪ ኃይሎች ቡራኬ ይገኝ ይመስል በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን እያሳሳተ ነው። በታሪክ እንደተረጋገጠው ለብሄራዊ ነፃነት የሚደረግ ትግል በልመና የሚገኝ አይደለም። አገራችን ከአንዴም ሁለቴም የተደፈረውን ብሄራዊ ነፃነቷን ያስከበረችው በልመና አይደለም። ብዙ መስወዕትነትን በጠየቀ የእናቶቻችንና የአባቶቻችን ትግል አማካይነት ነው። በዛሬው ዘመን የሚደረገው ትግል ደግሞ ከዚህ የበለጠ ሲሆን ሳይንሳዊ መሳሪያን የሚሻና ከዚህም በመነሳት የተወሳሰበውን የዓለም አቀፍ ፖለቲካ በቅጡ መረዳት የሚጠይቅ ነው። አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር በዛሬው ዘመን የብዙ አገሮች ብሄራዊ ነፃነት በቀጥታ ወረራ የሚደፈር ሳይሆን በማባበል አፈቀላጤዎችንና የወስጥ አርበኞችን በማዘጋጅት ነው። ለዚህ ደግሞ የተዘጋጀ ፣ ብሄራዊ ነፃነትን የሚቀናቀን ቲዎሪና ርዕየተ ዓለም አለ። በዚህ አማካይነት በላፉት ሃምሳና ስድሳ ዓመታት የብዙ ሶሰስተኛው ዓለህም አገሮች ብሄራዊ ነፃነት ተደፍረሮ ህዝቦች ወደ ባሰ ድህነት ተገፍትረዋል። የአገራችንም እጣ ከዚህ ውጭ አይደለም። ከዚህ ውጭ ማሰበና ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን ድህነትና ረሀብ እንዲሁም ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀል ከብሄራዊ ነፃነት መደፈር ጋር አለማግያያዝ መሞከርና ሰፊውን ህዝብ ለማሳሳት መሞከር የታሪክ ወንጀል እንደመፈጸም ይቆጠራል። ከዚህም ስንነሳ የሚደረገው ትግል ጸረ ወያኔ ብቻ መሆን የለበትም። ትግላችን ውስብስብና የቲዎሪና የሳይንስ ብስለትን ሲጠይቅ ፣ ይህ ደግሞ በየጊዜው ስትራቴጂያዊ በሆነ መልክ እየተነተነ መቅረብ አለበት። ይህ ማለት ግን ትግላችን ፍጥጫን ያዘለ ነው ማለት አይደለም። እንደድሮው ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል እያልን መፈክር ይዘን እንውጣ ለማለት አይደለም። በአንድ በኩል በቴዎሪና በኢምፔሪ የተደገፈ ትንተናና ከዚህ በመነሳት የትግልን አቅጣጭ መቀየስ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጀብደኛ ትግል ማካሄድ የተለያዩ ሁለት መስመሮች መሆናቸውን ከመጀመሪያውኑ ማወቅ ያሰፈልጋል።

ከዚህ ስነነሳ በአንዳንድ ግለሰቦች አማካይነትና የውጭው አመራርንም ጨምሮ የኢትዮጵያን ህዘቦች ዕውነተኛ የብሄራዊ ነፃነት ምኛትና ትግል እንዲሁም ደግሞ ባህላዊ አገር የመመስረቱን ጉዳይ ከግሎባላይዜሽን ውጭ ሊታሰብ አይገባም እየተባለ የሚለፈፈውና አገራችንን በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጉያ ስር ወድቃ እዚያው በዚያው እንድትታሽ የሚደረገው አሻጥር ከአሁኑ መቀጨት አለበት። ወያኔን ከጣልክልን ከወያኔ የበለጠ አንተ በዓለም አቀፍ ደረጃ የምታካሄደውን የፀረ ቴሮሪስት ትግል የበለጠ ከጎንህ ቆመን እንዋጋለን

የሚለውን የተሳሳተ አባባል ከአሁኑ በእንጭጩ እንዲቀጭ ማድረግ የማንኛውም አገር ወዳድና ዲሞክራት የታሪክ ኃላፊነት ነው።የዛሬው ትግላችን ሳንወድ በግድ ከወያኔ ጋር ብቻ ሳይሆን ከነዚህ የወስጥ አርበኞች ፣ የታሪክንና የአንድን ህዝብ ዕውነተኛ ብሄራዊ ነፃነት ፍላጎት ከማይገነዘቡ ጋርም ሊሆን ነው ማለት ነው። ይህን አቀራረብ እንደ ፋክክርና ወደ ጠብ የሚያመራ አደርጎ መመወሰድ የለበትም። ነገሮቸን እንድንረዳና የትግሉም አቅጣጫ እንዴታና ምን መሆን እንዳለበት ለማመልከት ብቻ ነው። ከዚህ ስንነሳ ስለኢትዮጵያም ሆነ ስለ ዓለም አቀፍ ፖለቲካ የተለያየ አመለካከት አልን የሚሉ ሁሉ በግልጽ ወደ ውጪ ወጠተን እንከራከር። አቋማችንን በግልጽ እናሳይ። በዚህ መሰረታዊ ጥያቄ ላይ አለመግባባት ካለ ሁሉም እንደ ፈለገው እየተነሳ የሚዘላብድበትና ህዝብን የሚያሳስትብትን ሁኔታ ፈጠርን ማለት ነው። ዛሬ በየፓል ቶክ ውስጥ ገብቼ የምሰማው ዐይነት ዝብርቅሩ የወጣ አስተሳሰብና ጩኸት።

በአንዳንድ አጋጣሚ ወቅት በፓል ቶክ ውስጥ ገብቼ ስሰማና የራሴንም አስያየት ስሰነዝር የምገነዘበው በመሰረቱ አንዳንድ የሀሳብ ልዩነቶች ቢኖሩም ፣ ችግሩ የመነጨውና የሚመነጨው ፖለቲካ የሚለውን መሰረተ ሀሳብ ከግንዛቤ ውስጥ ያለገባ ክርክር እን ደሚካሄድና ፣ በብዞዎችም ዘንድ ክፍተኛ የዕውቀት ማነስ ፣ የነገሮችን ሄደት በሚገባ ከሁሉም አቅጣጫ ለመመርመር ያለመቻል እንዳለ ነው። ብዙዎች ወያኔን እንቃወማለን ፣ ቅንጅትን እንደገፋለን ቢሉም የየግለሰቦችን ታሪክ ፣ የድርጅቶችን አመጣጥና በኢትዮጵያ የነጻነት ትግል ውስጥ የነበራቸውን ሚና ፣ የአፄው አገዛዝ ትቶ የሄደውን የተወሳሰበ ሁኔታና ለዛሬው ምስቅልቅል ሁኔታ የቱን ያህል አስተዋጽዎም እንዳበረከተ በፍጹም ግንዛቤ ውስጥ ማግባት ካለመቻል የመነጨ ነው። ሌላውም የራሱን ሃሳብ ረጋ ባለ መልክ መሰንዘር ሲጀምር ወደ ማስፈራራትና በቀይ ምልክት ሰርዞ ማባረር ፣ ወይም ደግሞ እጅግ በጋጠ ወጥ መልክ ጣልቃ ገብቶ ሌላ ነገር አለብን በማለት ሰው የጀመረውን ሃሳብ አንጠልጥሎ መስመሩን መዘጋት የተለመደ ሆኖ መጥቷል። ይህ ሁኔታ አንዳንዶቻችንን ግራ አጋብቶናል። ማስተማር የሚቻልብትን ሁኔታ እንዳንጠቀምና ሃሳባችንን እንዳናሸራሸር አድርጎናል። በእርግጥ እዚህ ላይ ሁሉንም መወንጀል አይቻልም። አንዳንድ መድረኮች ቀስ በቀስ ወደ በሰለ ውይይት እንደ ተሸጋገሩና ወደፊትም እንደሚማሩ ግንዛቤ እንዳለ መታወቅ አለበት። እስካሁን ድረስ በአክረሪነት ጩኸቱን የሚያሰማውና የሌሎችን አስተያየት ለመቀበል ከማይፈልገው አንድ የውጪውን አመራር እድግፋለሁ ብሎ እዚህና እዚያ ከሚሯሯጠው የፓል ቶክ መስመርና የወያኔን ፖለቲካ አቀባብቶ በሲቪክ ህብረተሰብ አሳቦ የሚያወናብደው በጣም የተደናቆረ ክፍል በስተቀር ሌሎችን መስመር ማሲያዝና ነገሮችም በጩኸት መልስ እንደማያገኙ ፣ በጥናት ላይ የተመሰረተ ውይይት መታለፍ የማይገባው የውይይትና የመፍትሄው መንገድ መሆኑን ማስገንዘብ ይቻላል። አንዳንዶች ይህንን እየተረዱ መጥተዋል ማለት ይቻላል።

ያም ሆነ ይህ እንደዚህ ዐይነቱ የተዘበራረቀ ትግልና መጯጯህ ትግሉን ሲያዘበራርቅ ፣ ለየዋሁና ለአገር ወዳዱ ደግሞ ግራ የሚያጋባ ሆኖበታል። ሀቀኛውን ከውሸታሙ ፣ አገር ወዳዱን ከአጭበርባሪው ለመለየት አዳጋች ሆኖበታል። በሳይንስ ያልተገራ ትግል የበላይነትን በመያዝ ወጣቱን ሁሉ የማይሆን ስሜቱን ቀስቅሶበታል። በዚህ የተሳከረው አወናባጅ ኃይል ወደ ፊት ከመሸምጠጥ በስተቀር ቆም ብሎ ጥያቄ ለመጠየቅ ፋታ ሳያገኝ ይቀራል። ብቻውን የሚጓዝና ብቻውን የሚያሸነፍ ነበር የሚመስለው። የሌሎች ጩኸት የማይሰማው ፣ በራሱ ዓለም ውስጥ የሚሸከረከርና ፣ ዛሬ ከዚኽኛው ነገ ደግሞ ከዚያኛው ጋር በመሰለፍ ትግልን የሚያምታታ ነው። ይህ ዐይነቱ የትግል ዘዴ ሰብሳቢ ከመሆን ይልቅ በታኝ ሆኗል። እን ደነቀርሳ በሽታ የሚሰረስርና ትግልን የሚያዳክም ነው። በሳይንስና በጥናት ላይ ያለተመሰረተ ትግል ዞሮ ዞሮ ወደ ድል አያመራምና።

ይህ ሁኔታ የሚያሳየን በየጊዜው የሚለዋወጠውን የኃይል አሰላለፍና የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ደካማ ሁኔታ ነው። አብዛኛው ከአገሩ ወጥቶ ውጪ አገር ለብዙ ዐመታት ቢኖርም

በከበርቴው ህብረተሰብ ውስጥ ራሱን ለማዋሃድና አዲስ የአኗኗር ስልትና ትግል ሊቀስም በፍጹም አልቻለም። ስለሆነም ልክ በጉዞ ላይ ይመስል እዚህና እዚያ በመክነፍ በእዚህ ዐይነቱ ትግል ውስጥ ቶሎ ብሎ የግንባር ቀደምትነትን ሚናን በመጫወት የሰከነ አመራር እን ዳይሰጥ ትግሉን ማዘበራረቅ ይጀምራል። ከዚህም ከዚያም ያልሆነ ኃይል ሰብስቦ ተሳስቶ አሳሳች እየሆነ ነው። ዛሬ የደረስንበት ሁኔታ ይህ ነው። አቅጣጫው የማይታወቅ የትግል ስልት !

## የተለያየ የትግል የህይወት ታሪክ ፣ የተለያየ አመለካከት

ለዛሬው መወናበድና ወደ አምላኪነት ባህርይ ማምራት በአንድ በኩል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የኢትዮጵያን ህዝቦች ትግል በአንድ መስመርና አቅጣጫ እንዳይጓዝ ማድረግና በውይይት የተመሰረተ ሁሉንም የሚያካትት የተቀናጀና በተወሰነ ፕርንሲፕል ላይ መስራት በሚለው ከተወሰኑ ድርጅቶች መሀከል የሚሰነዘረውን እስተያየት ማገድ ፣ ይህ የተለያየ የትግል ዘዴና አክራሪነት ፣ እንዲሁም ደግሞ ዲሞክራሲያዊ መሰረተ ሀሳቦችን ጥሶ በመሄድ እኔ ብቻ ነኝ መሪው ማለት የየድርጅቶችንና ግለሰቦችን የትግል ህይወት ታሪክና የዲሞክራሲ ግንዛቤ ልዩነት ያረጋግጥልኛል። የየግለሰቦች እርስ በርስ መናቆር ፣ ስም መጠፋፋትና የድርጅትን ሀብት ዘርፎ መሄድ ይህ ሁሉ የሚያረጋግጥው ሀቀኝነት እንደሚጎለን ፣ ዲሞክራሲያዊ ባህል እንደሌለንና ትልቁን ኃላፊነት የሚጠይቀውን የህብረተሰብ ግንባታ በትከሻችን ላይ ተሸክምን የህዝባችንን ጥያቄ ለመፍታት እንደማንችል ነው።

የዛሬው የትግል አቅጣጫ ደብዛው መጥፋት ፣ የርስ በርስ ሽኩቻ ፣ አለመደማመጥ ፣ በአን ድ በኩል የህብረተሰባችን ሳይንሳዊና የምርምር ባህል እንዲያም ሲል ጥያቄዎችን እያነሱ ዲሞክራሲያዊ ባህል ያለማደበር ነፀብራቅ ሲሆን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የየደርጅቶችን የተለያየ የፖለቲካ ባዮግራፊና ከረጅሙ የትግል ታሪክ አለመማር ጋር የተያያዘ መሆኑን ወዲያውኑ መገንዘብ ያቻላል። አሁንም እንደድሮው ፣ በተለይም ግለሰቦችን የሚያመልኩና በየብሄረሰቦቻቸው ስር መሽገው "ህዝቦቻችችንን ነፃ እናወጣለን" የሚሉ እንደድሮው አሁንም በጠባብ ስሜት በመወጠር ፣ የህዝብን ነፃነት ራሳቸው በነደፉት የትግል አርማ ውስጥ በማሽከርከር ከአርባና ከሰላሳ ዓመታት ትግል ምንም ትምህርት ለመቅሰም ያለመቻላቸው ነው። እራሳቸውን ኋላ ቀር ከሆነ አስታሳሰብ ሳያወጡ ፣ ሌላውን አታሳየኝ ከሚለው ፌሊጣቸው ሳይለቀቁ ፣ ከሌላው ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጠው መከራከር የማይችሉና ተምረው ማስተማርን ባህል ለማድረግ ያልቻሉ አሁንም እንደቀድሞው አጥፍቶ በመጥፋት ህልማቸው እየዋኙ ይገኛሉ። ታሪክን በማጣመም ፣ ያቺ አገር ለነሱ ብቻ ተፈጥራ የተሰጠች ይመስል የሌላውን ኢትዮጵያዊ ነፃነትና በሰላም ለመኖር ያለውን ፍላጎት እጨልሞ ለመኖር ከውጪ ኃይሎች ጋር በመተባበር የሚያደርጉት የጥፋት ትግል ተምረው የደነቆሩ ለምንም የማይበጁ ናቸው። ዘለዓለማቸውን በጥርጣሬ የሚኖሩ ፣ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ይልቅ ዕምነታቸውን በውጪ ኃይሎች ላይ በመጣል ችግርን በመፍጠር ትግሉን ውስብስብ የሚያደርጉ ናቸው። ግራ የገባቸው ፣ በየጊዜው እንደ እስስት ቀለማቸውን በመቀያየር ግራ የገባው ትግል የሚያካሂዱ ናቸው። እነዚህን በብሄረ-ሰብ ስም የሚነግዱ ኃይሎች ለማሳመንና ዕውነተኛውን የነፃነት ፌለግ ላማስተማር እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል። ዌብ ሳይታቸውን ለተመለከተ አሁንም እንደ ቀድሞው የሚያስታገቡት መፈክር የታሪክን ጎማ ወደ ኋላ ለመጎተት የሚደረግ የደንቆሮዎች ትግል እንጂ በምንም ዐይነት ግለሰብአዊ ነፃነትን የሚያቀዳጅና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን የሚያመጣ አይደለም። የሚገርመው እነዚህ በየብሄረሰቦቻቸው ጉያ ስር የተሰገሰጉ ኃይሎች በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲሉ የከረሙ ነበሩ። በሌላ አነጋገር የደርግ ካድሬዎች የነበሩና አንዳንዶችም ከፍተኛ ስልጣን የነበራቸው ነበሩ። በዚህ በተጣመመ አስተሳሰባቸው ፣ አክራሪነታቸውና ጎታች አመለካከታቸው ህዝባቸውን ነፃ ሊያወጡ ይችላሉ ወይ ?

ይህ ጉዳይ ነው ዛሬ ትግሉን ውስብስብ የሚያደርገውና ፣ በተለይም ተማርን የሚለውን ኃይል ጭንቅላቱን ጨምዶ ከያዘው ኋላ ቀር አመለካከት ማለቀቅ የሚያስቸገረው። ይህ የተበላሸ የፖለቲካ ቢዮግራፊን ለማስተካከልና ግለሰቦችንም ሆነ ድርጅቶችን ሰው መሆናቸውነ እን ዲገነዘቡ ለማድረግና ወደ ቀናው መስመር ተመልሰው ታሪካዊ ሚናቸውን እንዲወጡ ላማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። ለዚህ የሚያዋጣው ትግል ወደ ፊት ገፍቶ በመሄድ በቴዎሪና በሳይንስ ዕርቃናቸውን ማሰቀረት ብቻ ነው። ምክንያቱም እነዚህን ኃይሎች ለዘለዓለም እሽሩሩ ማለት ትግሉን የሚያድበስብስና የነፃነቱንም ዘመን የሚያራዝም በመሆኑ ነው። በተጨማሪም ደግሞ መታወቅ ያለበት አንድ ድርጅት ተነስቶ ይህንን ብሄረሰብ ወክላለሁ ሊል አይችልም። ግለሰቦች ሊሰባሰቡና ድርጅትን ሊመሰርቱ የሚችሉት በአንድ ርዕይና ህብረተሰብአዊ ዕሴት አካባቢ ብቻ ነው። ብሄረሰብን ነፃ አወጣለሁ የሚለው ከፖለቲካ ቲዎሪና ከሳይንስ ጋር በፍጹም አብሮ ሊጓዝ አይችልምና።ምክንያቱም ብሄረ-ሰብ ርዕይ ወይም የፖለቲካ ዕሴት አይደለምና ነው። አንድ ህዝብ ዕውነተኛ ነፃነቱን የሚቀዳጀው በሳይንስ ላይ የተመረኮዘ ትግል ሲያካሂድና ለስራ ሲዘጋጅ እንጂ ጥላቻን የትግል መፈክር በማድረግ አይደለም። ስለዚህም የብሄረ-ሰብ ነፃነት ታጋዮች ነን የሚሉ ከዚህ አገርን ከሚያፈራርስና ህዝብን ወደ ድህነት ከሚወረውር ትግላቸው መለቀቅ አለባቸው። ከኤርትራው የፃነት ትግል ትምህርት መቅሰም አለባቸው።

ከዚህ ስንወጣ ፣ ሌለው አስቸጋሪ ጉዳይ ደግሞ በዚህም በዚያም ብለው የፖለቲካ ካድሬነት ሚና ሲጫወቱ የነበሩትን መልክ ማሲያዝ ነው። እነዚህ ኃይሎች በአንድ በኩል ወያኔን የሚጠሉና የኢትዮጵያን አርማ አንግበው ለአንድነት እንታገላለን የሚሉትን ያጠቃልላል። የእነዚህ ሰዎችም ችግር በጣም የተጣመመ የፖለቲካ ቢዮግራፊ መኖር ሲሆን ፣ ከ15 ዓመት በኋላም እራሳቸውን በአዲስ አስተሳሰብ ሊገነቡ ያልቻሉ ናቸው። አንዳንዶቹ አሁንም አመጽ የሚቃጣቸውና ለዲሞክራሲያዊ ውይይት ዕድል የሚሰጡ አይደሉም። ሰውን በጥርጣሬ የሚመለከቱ ፣ ስለሰው ልጅና ነፃነት ያላቸው አስተሳሰብ እጅግ የተጣመመ ፣ ሰውን የሚን ቁና ግለሰቦችን የሚያመልኩና በራሳቸው ላይ ዕምነት የሌላቸው ናቸው። ዛሬ ለዕውነተኛ ነፃነት የሚደረገውን ትግል የሚያደናቅፉና በጭፍን ወደ ፊት የሚገፉ ፣ ቢያመቻቸውም ሰው እየጨፈለቁ ለመሄድ የሚፈልጉ ናቸው። እነዚህም እንደ ብሄረ-ሰብ ነፃ አውጪ ነን ባዮች በራሳቸው ክልል ብቻ የሚሽከረከሩ ለትግል የሚያስፈልገውን ዲሞክራሲያዊ ባህል ለማዳበር በፍጹም የማይፈልጉ ፣ በዚህም በዚያም ብለው የሚሽለኮለኩና መንገዱን የሚዘጉ ናቸው። ከሌላው ጋር ለመተባበር የማይፈልጉና የአንድን ህዝብ የተለያዩ እሴቶች መኖርና እንዲሁም ደግሞ የሌሎችን የነፃነት ፈለግ ለማዳመጥና ሌላም የትግል መንገድ እንዳለ ለመስማት የማይሹ ናቸው። እነዚህ ናቸው ዛሬ የፓልቶክ መድረኩን ይዘው ሰው አላናግርም የሚሉና ብዙ ቀና ሰዎችን የሚያሳስቱ። በዚህ ዐይነቱ ትግላቸው ቅንጅት የምህሮች ስብስብ እን ዳይሆን በሩን እየዘጉና እንዲያም ሲል ፊዩዳላዊ የቤተሰብ መድረክ እያደረጉት ነው።ጠጋ ብለን እንዳየነው የእነ ኮለኔል መንግሰቱን ዐይነት የማራቅና የማስጠጋት ፖለቲካ እየተጫወቱ ጠቅላላቅው ትግል ምሁራዊ ፈለግ እንዳይዝ የታሪክ ወንጀል እየሰሩ ነው። ከዚህ ውጪ ቅን ጅትን የሚደግፉ ግን ደግሞ የውጪውን አመራር የማይቀበሉ በአሰተሳሰባቸው ቀና የሆኑ ግን ደግሞ ትክክለኛው የፖለቲካ መስመር የትኛው እንደሆነ ግራ የገባቸው አሉ። እነዚህ በአስተሳሰባቸው የለዘቡና ለአገራቸው ቀና አስተሳሰብ ያላቸው ናቸው። ሰው የሚለውን በጨዋ መልክ ለማዳመጥ የሚፈልጉ ናቸው። ይሁንና ግን ያለፈውን ውስብስብ ትግል ለማስረዳት ደግሞ በጣም አሰቸጋሪ ሁኔታ እንዳለ መታወቅ አለበት። ያም ሆነ ይህ ዲሞክራሲያዊ ባህልን ለመከተል የሚሹና በስነ ስርዓትም ለመወያየት ዝግጁ እንደሆኑ መገን ዘብ ይቻላል።

ከዚህ ውጪ ያለው ሌላው ኃይል በዚህም በዚያም ብሎ የቲዎሪና የሳይንስ ጥራት ሳይኖረው ቀስ በቀስ ባገኘው ዝና ለጠራ ትግል ያማያመች ሁኔታ በመፍጠር ላይ ነው። ይህ ኃይል ያለው አመለካከት እጅግ የተዘበራረቀ ከመሆኑ የተነሳ የዓለምን የፖለቲካ ሁኔታ በቅጡ ሊገነዘብ የማይችልና አሜሪካንን በመማፀን ነፃነት የሚገኝ የሚመስለው ፣ እዚያው አሜሪካ እየኖረ እዚያ ምን እንደሚሰራ በፍጹም የማይረዳ ነው። ዓለምን እንደፈለግሁት

አሸከረክራለሁ ከሚል ኃይል ፣ እዚህና እዚያ በሰው አገር ጣልቃ እየገባ ጦርነት ከሚያካሂድ መንግስት ምን ቀና ነገር እንደሚገኝ በፍጹም ሊገነዘብ የማይችል ሌላውን የዋህ ኢትዮጵያዊ የሚያሳስት ነው። የፖለቲካ ስልቱ የተምታታበት ኃይል በመሆኑም በዚህም በዚያም ብሎ ኃይልን ሊበታትን የሚችል ነው። እዚህ ላይ ያለው ችግር ሌሎችን ማሳሰቱ ብቻ ሳይሆን ፣ የሚሳሳተው ኃይል ዛሬ በአገራችን የሰፈነውን የጭቆና አገዛዝ ከአሜሪካ የመስፋፋትና የአገሮችን ነፃነት ከመርገጥና የስልጣኔውን ዘመን ለማራዘም ከሚደረገው ትግል ጋር አጣምሮ ለማየት ያለመቻል ነው። በዚህም የተነሳ ሺህ ጊዜ መለማመጫ የሀዘን ደብዳቤ ለአሜሪካ መንግስት በመጻፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሊሰፍን ይችላል ብሎ የተገነዘበና የኢትዮጵያ ህዝቦች የነፃነት ዕድል በአሜሪካን የተቀደሰ ቡራኬ ሊገኝ የሚችል አድርጎ ግንዛቤ ውስጥ ያሰገባ ነው። ይህኛውም እንደሌሎች አክራሪ ባይሆንም የሌላውን አስተሳሰብ ለመቀበልና የዓለምን የተወሳሰበ ሁኔታ ለመረዳት ያለው ችሎታ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ከትቶታል። ሁኔታው ወዴት እንደሚያመራ ግራ የተጋባና በቀላሉም ሊገባውም የሚችል አይደለም።

ከዚህ ጋር በመያያዝ ፣ አንዴ በተቃዋሚ ወገን በመሰለፍና የዛሬውን አገዛዝ እያወገዙ በሌላ ወገን ደግሞ የእርቅ ፖለቲካ እናድርግ የሚለው ኃይል ለዲሞክራሲ ያለው ፍላጎት የሚያጠራጥር ባይሆንም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚያካሂደው በየጊዜው ተለዋዋጭ ጥሪ ትግሉን አስቸጋሪ እያደረገውና ውኻንብር እየነዛ መሆኑን መታወቅ አለበት። የሚደረገው የዕርቅ ጥሪ የዛሬውን አገዛዝ በፍጹም ርህራሄ እንዲኖረው የሚያደርግ አይደለም። እንደዚህ ዐይነቱ የፖለቲካ ትግል የከረረና ፣ አገዛዙ የኢትዮጵያን ህዝቦች ረግጦ ለመግዛት ቆርጦ ከተነሳ ሰንብቷል። የራሱ የሆነ የኢኮኖሚ ኃይል ገንብቷል። ዲሞክራሲያዊ ባህል የለውም። ክርክርንና ውይይትን ባህሉ ያደረገ አይደለም። የሰብአዊነት ባህርይ የሌለው ነው። ስንትና ስንት ሺህ ህዝብ በረሀብና በድህነት ሲረግፍ ዝም ብሎ የሚመለከት ነው። ጠቡ ዛሬ በባልና በሚስት መሀክል ፣ አንተም ተው አንቺም ተይ በሚል ዐይነት ማስታረቅ የማይቻልበት ሁኔታ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ እንደዚህ ዐይነቱን የፖለቲካ ትግል በዕርቅ ፖሊሲ ማረጋጋት በፍጹም አይቻልም። የራሴን ኢምፓየር መስርቻለሁና ታግላችሁና አሸንፋችሁ ስልጣን ውሰዱ የሚል አመጽን ባህሉ ያደረገ ኃይል ነው ዛሬ ያለው። ሁኔታው ይህ ከሆነ ለምንድነው እየመላለሱ ዕርቅ መደረግ ያለበት ዛሬ ነው እየተባለ የማያስፈልግና አሳሳች ዘመቻ የሚካሄደው። የፖለቲካ የዋህነት ወይስ ሌላ የትግሉን ትጥቅ የሚያስፈታ መሰሪህ ? ለመገመት በጣም አስቸጋሪ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ይህ ግለሰብ አሁንም እንደወትሮው በሰላም ትግል ያምናል። ጥያቄው ምን ዐይነት የሰላማዊ ትግል እናድርግ የሚል ነው። እነ ደዚህ እያልን ተቃዋሚ ነን በሚለው ሰፈር ያለውን እርስ በርሱ የሚጋጭ የትግል ስልት መጥቀስ ይቻላል። በሌላ ወገን እንደዚህ ዐይነቱ የተዘበራረቀ የትግል ስልት የተቃዋሚውን የፖለቲካ ብስለት ደረጃ የሚያመለክትም እንደሆነ መገንዘብ ያሻል። እዚህም እዚያም የተሰበጣጠረ ኃይል እኔም ትግል አራምዳለሁ እያለ እንደፈለገው ሲዋኝ ለአገዛዙ የመጠናከሪያ ስትንፋስ እየሰጠው እንደሆነ መታወቅ አለበት።

ዛሬ ያለው ሌላው ፍጥጫ በህብረትና በቅንጅት መሀከል ሲሆን ፣ በህብረቱ ውስጥ የፖለቲካ ተዋናዮች ከድሮው የግራ ንቅናቄ የፈለቁና ከሌሎች ይልቅ በአስተሳሰባቸው የተሻለ ጥራት ያላቸው ናቸው። የህብረት ችግር ግን ኃይልን ሰብስብ አድርጎ ሰፊ ትምህርት ለመሰጠት ወደ ውጭ ግፊት ለማድረግ ያለመቻል ነው። ከሌሎች በሚመጣው ግፊት በመዋዋ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ያለውን አማራጭ መንገድ ለማሳየት ያለውም የሰው ኃይል ካለው የኢዮጵያ የተወሳሰበ ችግር ጋር ሊመጣጠን የሚችል አይደለም። ሌላው ችግር በድሮው ዓለም የመኖር አዝማሚያ ሲታይ ፣የድሮውን ህልም አሸንቀዋሮ ጥሎ ወደ ፊት ለመጓዝ አማካይ መንገድ ላይ ወይም አሰቸጋሪ መንገድ ላይ ይገኛል። ይህ ከድሮው ተጎትቶ የመጣ ህልምና በዚያ ዓለም ውስጥ መኖር ኃይል እንደሚጨርስ በብዘዎች ዘንድ ግንዛቤ የተገባ አይመስልም። ይሁንና በትዕግስት ከነዚህ ጋር ሊደረግ የሚችለው ውይይትና ክርክር መንገዱ ክፍት ሲሆን የምሁር ልምድም እንዳለ መገንዘብ ይቻላል።

አጠቃለዩን የተቃዋሚውን ጎራ ስንመለከት ያለው አጠቃላይ ችግር እራሳችንን ለማወቅ ያለው ችግር ፣ ለኢትዮጵያ የሚጀውን የትግል ፈለግና ምን ዓይነት ህብረተሰብስ ሊመሰረት ይችላል በሚለው ላይ አሁንም ቢሆን አጠቃላይ ስምምነት ያለ አይመስልም። ይህ ሳይንሳዊ ትግልን መመሪያ ለማድረግ ያለመቻል ልምድ በብዙ መሰረተ ሀሳቦች አለመግባባት እንዲፈጠር ሲያደርግ ፣ የትግሉን አቅጣጫም መስመር ለማሲያዝ የዚያኑ ያህል አስቸጋሪ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። እነዚህን ዘርዘር አድርገን እንመለክት።

## የማንግባባቸው መሰረተ-ሀሳቦች ግን መረዳት ያለብን ጉዳዮች

በመጀመሪያ ለአንድ ህዝብ እንደ ህብረተሰብ ሆኖ ለመኖርና በፀና መሰረት ላይ ተግንብቶ ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ የሚቀጥሉት መሰረተ-ሀሳቦች ጭንቅላት ውስጥ መቋጠርና የትግል መመሪያዎች መሆን አለባቸው።

1ኛ) የህብረ-ብሄር አመሰራረት ጉዳይ ፤ እዚህ ላይ ኢትዮጵያ እንደ ህብረ-ብሄር ተጠናቃ ያለች አገር ነች የሚለው ጉዳይ በብዞዎቻችን ዘንድ ግንዛቤ ውስጥ የገባ አይደለም። እያን ዳንዱ አገር እንደ አንድ ህብረ-ብሄር ለመኖር ከቋንቋና ከባንዲራ ባሻጋር ሰፊ የሳይንስና የቴክኖሎጂ መሰረት እንዲኖረው ያስፈልጋል። ጠቅላላው ህብረተሰብ በስነ ስርዓት እንዲኖር ከተፈለገ ህዝቡ በስራ ክፍፍልና በስራ መወጠር ፣ የመፍጥር ችሎታውን ተግባራዊ የሚያደርግበት ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። በዚህ ላይ ደግሞ ህዝቡን የሚያስተሳስር ባህላዊ ዕሴት መኖር አለበት። ሰፊ የመመላለሻና የመገናኛ መንገድ መዘርጋት አለበት። ከተማዎች መገንባትና በየጊዜው መሻሻል አለበቸው። ይህ በሌለበት አገር ውስጥ አንድ ህዝብ እንደ ህብረተሰብ ሊያያዝ አይችልም። እስከዛሬ ድረስ በብዙ የኢትዮጵያን ባንዲራ አንጠልጥለው በሚታገሉ መሀከል ያለው አለመግባባት ግልጽ ያልሆነው ነገር ለአንድ ህብረ-ብሄር መመስረት አስፈላጊ የመሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎችን ለመገንዘብ ያለመቻል ነው። አንዳንዶቹ እንዲያውም አልፈው ተርፈው ኢትዮጵያ በጾም በጸሎት የምትኖር ነው የሚመስላቸው እንጂ አንድ ህብረ-ብሄርን ለመገንባትና ተከታታይነት እንዲኖረው ለማድረግ የማያቋርጥ ትግል ማድረግ እንደሚያስፈልግ አያምኑም። በብዞዎቻችን ዘንድ ያለው ግንዛቤ እጅግ አስቸጋሪና በጥሞናም ለማስረዳት ከባድ ነው።ተቀባይነት ስሌለ። ይህ መሰረተ ሀሳብ አንደ መቋጠሪያ እስካላገኘ ድረስ ለነፃነት የሚደረገው ትግል እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል ፣

2ኛ) ከዚህ ስንነሳ ብዙዎቻችን ዘንድ የዓለም ኮሚኒቲው በሚባለው ላይ ያለን አመለካከት ግራ የተጋባ ነው። በብዞዎቻችን ዘንድ ይህች ዓለም ውድድር የማይደረግባት ፣ አንዱ ሌላውን ጭራ ለማድረግ ወይም ደግሞ ለመዋጥ የማይወዳደርባት ፣ ነፃነት በቡራኬ ወይም ደግሞ በሰከነ ፖለቲካና በልምምጥ የሚገኝ የሚመስላቸው ብዙ የዋህ ኢትዮጵያውያን አሉ። የዓለምን የተወሳሰበ ትግል የማይረዱና ሊረዱ የማይፈልጉ ፣ እዚያው በዚያው እየታሹ ለመኖር እጃቸውን ወደ ላይ አውጥተው ተሸናፊነታቸውን እያረጋገጡ ኢትዮጵያን የዚህም ሆነ የዚያኛው ኃይል ጭራ ለማድረግ የሚራወጡ አሉ። በተለይም የአሜሪካ ጉያ ስር ጠቅልለው ቢገቡ ደስታውን የማይችሉትና ወያኔ ከሄደ ስልጣኑን ብቻ ለኛ ስጥን እንደፈለግህ እናደርግልሀለን የሚሉ ተወናብደው ሌላውን ግራ የሚያጋቡ በብዛት አሉ። ከሌሎች አገሮች የትግል ልምድ የማይግሩና የነፃነትን ትርጉም ሊገነዘቡ የማይችሉ። ስለሆነም በዚህ መስክ ግልጽ የሆነ አመለካከት ከሌለና ጥቂት ተዋናዮች ሰውን ግራ የሚያጋቡ ከሆነና የፖለቲካውን ም መድረክ እያጠበቡ ከሄደ የኢትዮጵያ ህዝቦች ነፃነትና ብልጽግና አዲዮስ ማለት አለብን። ትገሉ ውስብስብ ነው ማለት ነው።

3ኛ) አንድ ህዝብ እንደ ህዝብ ለመኖር የግዴታ ሰፊ የኢኮኖሚ መሰረት ያስፈልገዋል። ይሁን ና በብዙዎቻችን ዘንደ ያለው ግራ መጋባት የገበያ ኢኮኖሚ የሚለውን መሰረተ ሀሳብ ከብዙ

አቅጣጫዎች ለማየት ያለመቻል ነው። የገበያ ኢኮኖሚ ሲባል ንግድና መሸቀል የሚመስላቸው ያሉ ብዙ ናቸው። የገበያ ኢኮኖሚ ሳይንሳዊ መሰረት እንደሚያሰፈልገው ፣ ካለቴክኖሎጂና ካለኢንዱስትሪ የሚያድግና የሚስፋፋ የሚመስላቸው ብዙ የዋሀ ኢትዮጵያውያን አሉ። ከላይ የተጠቀሰት ሁለት መሰረተ-ሃሳቦች ከዚኽኛው ጋር በጥብቅ የተያያዙ መሆኖቻውን በፍጹም የማይረዱ አያሌዎች ናቸው። ስለዚህም በዚህ ላይም ግንዛቤ እስከሌለ ድረስ ለእውነተኛ ነፃነት የሚደረገው ትግል ደብዛው ይጠፋል ማለት ነው።

4ኛ) የብሄራዊ-ነፃነት ጉዳይ ፤ ብዘዎቻችን ስልብሄራዊ ነፃነት በምናወራበት ጊዜ ዳር ድን ደበርን እንደመነሻ አድርገን ነው። አገር ከቀተቆረስና ከተደፈረ በዚህ ብቻ የብሄራዊ ነፃነት መገርሰስ የሚገለጽ የሚመስላቸው ብዙ የዋሀ ኢትዮጵያዋን አሉ። ይህ አንደኛው ቢሆንም ፣ ለብሄራዊ ነፃነት መከበርና አለመደፈር ዋናው መሰረተ-ጉዳይ የውስጥ ኢኮኖሚው በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ መገንባት ፣ በልዩ ልዩ ባህል የዳበረ የተሳሰረ ህዝብ ፣ በጥሩ አርክቴክቸር የሚታይ የከተማ ግንባታ ፣ የሊትሬችር መዳበርና የሰፊው ህዝብ ንቃተ-ህሊና ደረጃ ፣ በአጠቃላይ ደግሞ የህዝቡ የማቴሪያል የኑሮ ሁኔታ... ወዘተ. እነዚህ በሌሉበት ፣ ባልተስፋፉበትና ባልዳበሩበት አገር ስለብሄራዊ ነፃነት ማውራት በፍጹም አይቻልም። በሚልዮን የሚቆጠር ህዝብ በድህነት ፣ በረሀብና በልምና በሚኖርበት አገር ውስጥ ስለብሄራዊ ነፃነት መከበር ማውራት አላዋቂነትም ብቻ ሳይሆን ብዙዎች ትርጉሙን በሰፊው ተረድተው ትግላቸውን እንዳያጣምሩና የተከበረች አገር እንዳይገነባ መንገዱን የሚዘጋና የተዝረከረከች አገር እንድትቀር ከማድረግ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው በፍጹም አይችልም። ብዙዎቹ በሰራዊት ብዛት ፣ በቢሮክራሲው መጠናከርና በጥቂት በናጠጡ ሰዎች ብሄራዊ ነፃነት የሚከበር የሚመስላቸው እንዳሉ በማደርጋቸው ውይይት ልገነዘብ ችያለሁ።

ለዚህ ብሄራዊ ነፃነትን ከሁለመንታው አንፃር ያለመረዳት ምክንያት ከብዙ ነገሮች ጋር የተጣመሩ ናቸው። ስለዕድገት የተዛባ አመለካከት ካለን ስለ ብሄራዊ ነፃነት የተሟላ አመለካከት በፍጹም ሊኖረን አይችልም። ስለ ሰው ልጅ ምንነት በደንብ ካልተገነዘብን እን ዲሁም ስለብሄራዊ ነፃነት ምንነት ልንረዳ በፍጹም አንችልም። የራሳችንን የኑሮ ፍልስፍና ከውጪ ኃይሎች ጋር አጣምረን የምናይ ከሆነ እንዲሁም ስለብሄራዊ ነፃነት ግልጽ የሆነ አመለካከት በፍጹም ሊኖረን አይችልም። ይህ ጉዳይ ደግሞ በዚህች ዓለም ላይ የመኖር ትርጉም ምንድ ነው ብለን ካልጠየቅንና ለአገራችንና ለህዝባችን ልናባረክት የምንችለውን በዕውቀት የሚገለጽ ሰፋ ያለ የህዝብ አኗኗር ስልት ከራሳችን ጋር ካላዋሃድን ስለ ብሄራዊ ነፃነት ምንነት ግንዛቤ ሊኖረን በፍጹም አይችልም።ባጭሩ የብሄራዊ ነፃነትን ትርጉም ከሰፊ የባህላዊ እንቅስቃሴ ጋር ካላያያዝን ስለ ብሄራዊ ነፃነት መከበር በፍጹም አፋችንን ሞልተን ማውራት አንችልም ማለት ነው። ዛሬ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ያለው ችግርም ይህንን በቅጡ ያለመገንዘብ ነው።

5ኛ) ከዚህም ስንነሳ በምን ዐይነት ዕውቀት ላይ ተመርኩዘን ነው አገራችንን መገንባት የምን ችለው የሚለውን ጥያቄም ስናነሳ ትልቅ ችግር ውስጥ እንገባለን። ዕውቀት በትምህርት ገበታ ላይ ብቻ የሚገኝ አይደለም። ይህ ቢሆንማ ኑሮ እስከዛሬ ድረስ እዚህ ውድቀት ላይ ባልደረስን ነበር። በሌላ አነጋገር ዕውቀት ማለት በየጊዜው ራሳችንን እንድንጠይቅ የሚያደርግና የታሪክን ኃላፊነት በመገንዘብ ለህዝባችን ነፃነት እንድንታገል የሚያደርገን መሰረታዊ ሀሳብ ነው። ከራሳችን በፊት ለህዝባችን የቆምን ፣ ለመጪው ትውልድ ታሪክን ሰርተን እንድናልፍ የሚያደርገን መሰረታዊ መመሪያ ነው። ዕውቀት ማለት ተፈጥሮን የምን ቃኝበት ፣ የተፈጥሮን ውበት እያደነቅን የምንከባከብበትና ቆንጆ ቆንጆ ነገሮች ለመስራት የምንዘጋጅበት መሰረተ ሀሳብ ማለት ነው። ባጭሩ ዕውቀት ማለት የኑሮን ተስፋ ማሳይት ፣ ዓለምን ከሁለንታዊው አንፃር የምንቃኝበት መሰረተ ሃሰብና አገራችንን በአዲስ መልክ የምን ገነባበት መሰረተ ሃሳብ ነው። ይህ ሲሆን በርግጥም ታሪከን መረዳት እንችላለን።

ይህንን የማነሳው ካለምክንያት አይደለም። ምክንያቱም በብዙዎች ዘንድ ዕውቀትን በሚመለከት አንድ ወጥ አሰራር ያለ ስለሚመስል ነው። ይህንን የምለው ብዙዎቻችን

በቀጥታ ከሚታዩን አልፈን ሌሎች ነገሮችን ለማየት ትግል ለማድረግና ወደ ተሰባሰበ ሀሳብ በመምጣት ስምምንትን ፈጥረን አንድ የተባረከችና የተከበረች አገር ለመመስረት ያለን ኃይል ለመጠቀም ያለን ፍላጎት ዝቀተኛ መሆኑን ምናልባት ባልሳሳት ስለምመለከት ነው።

እዚህ ላይ ላቁምና ዛሬ ጭንቅላታችንን ጋርዶ የያዘው ነገር ጥያቂ ለመጠየቅ ያለመቻላችን ነው። በመሰረታዊ ነገሮች ላይ ከመነጋገርና ጥናት ከማድረግ ይልቅ በአልባሌ ነገር ላይ ጊዜያችንን እናጠፋለን። በማያሰፈልግ ቦታ ላይ ጌዜያችንን እናባክናለን። እግዚአብሄር የሰጠንን ጭንቅላት በስነ ስርዓት እንዳንጠቀምበት የጋረደንን ነገር ለመግፈፍ ድፍረቱ የለን ም። በአጭሩ ራሳችንና የታሪክ ኃላፊነታችንን እንዘነጋለን። በዚህም ምክንያት የትግልን ትርጉም በማዛነፍ ወደ ማይሆን ግብ ግብ ውስጥ እንገባለን። ከዚህ ዐይነቱ ማጥ መውጣትና ታሪክን ለመስራት የግዴታ ራሳችንን መጠየቅ አለብን። እያንዳንዳችን ለራሳችን ህይወት ኃላፊነት አለብን። ማንም እኛን ሰው አያደርገንም። እያንዳንዳችን በራሳችን ላይ ዕምነት ሲኖረንና ዕውነተኛ ግለሰብአዊ ነፃነትን ከተረዳን ለህብረተሰብአችንም የምናደርገውን አስተዋጽዎ በደንብ መረዳት እንችላለን።

ዛሬ በመሀከላችን ያለው አለመግባባት የሚመነጨው ራሳችንንና የምንፈልገውን ካለማወቅ የተነሳ ይመስለኛል። እያንዳንዳችን በዚህች ዓለም ላይ ስንፈጠር ትርጉም እንዳለን ስለማን ረዳ ወደ አጉል ሽኩቻና መነካከስ እናመራለን። አገርን ወደ ሚያወድምና ታሪክን ወደ ሚያበላሽ። ትግላችን ለዚህ ወይም ለዚያኛው ድርጅት መሆን የለበትም።የሀገር ፍቅር እንጂ ለዚህ ወይም ለዚያኛው ድርጅት ታማኝ መሆን የለብንም። ለዚህ ደግሞ የፖለቲካና የህብረተሰብ ርዕይ ያስፈልገናል። ፍቅራችንና በስራ የሚገለጽ ፤ መስዋዕትነታችን ከአገርና ከህዝብ ጋር ብቻ ነው መያያዝ ያለበት። ይህ ሲሆን ከቡድናዊ ስሜት ባሻገር የየድርጅቶችን ሚናና የሚናገሩትንና የሚጽፉትን እያገናዘብን ሚዛናዊ ፍርድ ልንሰጥ እንችላለን። በመሀከላችን ዛሬ የጎደለን ለመደማመጥ ያለመቻል ነው። ለምንድ ነው አንዱ ከሌላው የተለየ የሚያሰበው ብሎ ለመጠየቅ ያለመቻል ነው። እራሳችንን ለመለወጥ ዝግጁ ካልሆን ፤ በየጊዜው ጥያቄ የማንጠይቅና የማንደማመጥ ከሆን ፤ ህዝባችን በዘለዓለማዊ ጨለማ ውስጥ እንዲኖር እንደራጋለን ማለት ነው። ይህ እንዳይሆን ከፈለግን የግዴታ ረሳችንን መጠየቅና በአዲሰ መንፈስ መነሳት ያለብን ጊዜ ዛሬ ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ በተወሰኑ መሰረተ ሃሳቦች ዙሪያ መሰብሰብ ፤ በዕወቀት ላይ የተመሰረተ ወደ ጠብ ያማያመራ ኢትዮጵያዊነትን ማዳበርና በንጹህ መንፈስ ለመስራት መዘጋጀት ነው። ያቺ አገር የሁሉም አገር መሆኗን ተገንዝቦ የጠባብ አመለካከትን ቆብ አሽቀንጥሮ በመጣል ወደ ግልጽ ውይይት ማምራትና አንድ ሁላችንንም ወደ ሚያስተሳስር ዐላማ መምጣት የጊዜው አንገብጋቤ ጥያቄ ነው።

በመሀከላችን መግባባት እንዲኖር ከተፈለገ ፤ አገራችንን ከጥፋት ለማዳን የጠበቀ ፍላጎት ካለን ስራዎቻችን ሁሉ የተወሰነ ፕሮፌሽናለቲ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ዛሬ እንደምናየው የአገራችንንም ሆነ ዓለም አቀፋዊዉን የፖለቲካ ሁኔታ እየተነተ ፤የስልጣኔውን ፈለግ እያሳየ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ዐይን የሚከፍትና የማሰብ ኃይላቸውን ሊያዳብር የሚችል ጋዜጣም ሆነ መጽሄት ታትም ሲወጣ አይታይም። ስለዚህም በየአስራአምሰት ቀን ወይንም በወር አን ድ ጊዜ እየታተመ ሊወጣ የሚችል ጽሁፍ መዘጋጀት አለበት። ለዚህ ደግሞ የግዴታ የገንዘብ ድጋፍና የተወሰኑ ሰዎች ፤ ቢያንስ አራት ያህል አንድ ቦታ የሚኖሩ መሆን አለባቸው። ጽሁፉ ፤ የታሪክ ፤ የስልጣኔ ፤ የፖዬዚ ፤ የፍልስፍና የፖለቲካና እንዲሁም የቲአትርና የአርክቴክተሮችን መልዕክት ይዞ የሚታተም ሲሆን ፤ ይህ የግዴታ ከአገራችን ሁኔታ ጋር እን ዲያያዝ ይደረጋል። ይህ ሲሆን ብቻና አዳዲስ ኃይል ማሰልጠን ስንችል ለአገራችን ዕደገትና ስልጣኔ እንዲሁም ተከብራ መኖር አስተዋፅዎ ማበርከት የምንችለው።

ፈቃዱ በቀለ /ከበርሊን